# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
# *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

(አንድነት/United)

ታህሣሥ 19 ቀን 2008 ዓ. ም
December 29, 2015

## የአምባገነኖች መቃብር ሲቆፈር

አምባገነን መንግሥታት ሁሉ ዋነኛ ሥነ-ባህሪያቸው ሥልጣን ከእጃቸው አፈትልኮ እንዳይወጣ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ነው። ይህንን እውን ለማድረግ መንግሥታዊ ኃይል በመጠቀም የሕዝብን የመሰብሰብ፣ የመደራጀት፣ ሃሳቡን በነፃ የመግለጽ፣ የመናገርና የመፃፍ መብቱን ይነፍጋሉ። ከዚህ በተጨማሪም ሕዝብን በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በዘር፣ በጎሣ፣ በቀየ፣ በሰፈርና መንደር፣ በአብሮ-አደግነትና የመሳሰሉት አስተሳሰቦች ሁሉ በመጠቀም አንድነቱን በሚያናጋ በከፋፍለህ ግዛው ተንኮል ይበክላሉ። የውጪውን ዓለም ለማታለል የሚጠቀሙበት ሌላው ዘዴያቸው ደግሞ በዴሞክራሲ ስም በመማልና በመገዘት አስመሳይ ዴሞክራቶች ሆነው በመታየት ነው። ከሕዝቡ ውስጥ ለሥልጣናቸውና ለሆዳቸው የተገዙ አድርባዮችን መልምለው የአገርንና የሕዝብን አንጡራ ሀብት እየዘረፉና እያዘረፉ ሰፊው ሕዝብ በረሀብ አለንጋ እየተጠበሰና መብቱም እየተረገጠ ዴሞክራሲያዊ አሠራር አለን ይላሉ። ሌላው የአምባገነኖች ባህሪ ደግሞ ከእነሱ በፊት የነበሩ የአምባገነን መንግሥታት ዕጣ-ፋንታ እንዴት እንደነበረ መማር አለመቻል ነው።

ኢዲ አሚን ዳዳ ከአፄ ቦካሳ አልተማረም እንዲሁም የኢንዶኔዥያው ሱካርኖ ከእርሱ በፊት ከነበሩት አምባገነኖች ጨርሶ ምንም ትምህርት አልገበየም። ህወሓት/ኢህአዴግም ከመንግሥቱ ኃይለማርያም አንዳችም ነገር አለመማሩን እያየን ነው። አምባገነኖች ሥነ-ልቦናቸው የታወረ በመሆኑ፣ የሥልጣን ማሰንበቻ ዘዴ ተጠቅመው እየተንገዛገዙ መቆየታቸውን እንጂ የታፈነ ሕዝብ የተዳፈነ እሳት መሆኑን በመረዳት አይቀጡ ቅጣት እንደሚቀጣቸው አያጤኑትም፤ አይገነዘቡትም።

በጠብመንጃ ኃይለ ሥልጣን ላይ የወጣው ህወሓት/ኢህአዴግ የውጭ ኃይሎችን ሊያታልል የሚችልበትን ሕገ-መንግሥት አውጥቷል። በዚህ ሕገ-መንግሥት ተብዬው ውስጥ የሰፈሩ

P.O.Box 91384
Los Angeles, CA 90009

Phone: 202- 241 2078
Email Address: eprp-united@eprp-ihapa.com

የዓለም-አቀፍ መስፈርትን ሊያሟሉ ይችላሉ የተባሉ ዓይነን የሚስቡ ነጥቦችን አጠቃሏል። ይሁንና እንደ አንቀጽ 39ና ሌሎችም አገር አጥፊ የሆኑ አንቀጾች መግባታቸውን መዘንጋት የለብንም። ይህ ሁሉ ሆኖ ህወሓት/ኢህአዴግ ያሰፈራቸውን ሕግጋት የሚጥሰው ሕዝብ ሳይሆን ራሱ መንግሥት ተብየው መሆኑ ግልጽ ነው። ለምሳሌ አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ አንድ "ማንኛውም ሰው መሣሪያ ሳይዝ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፣ አቤቱታ የማቅረብ መብትና ነፃነት አለው" ይላል። ነገር ግን ህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ምንም መሣሪያ ሳይዙ ሰልፍ በወጡና አቤቱታ ባቀረቡ ዜጎች ላይ በርካታ ጭፍጨፋዎችን አካሂዷል፤ የብዙ ሰው ሕይወትም አጥፍቷል፤ በጣም ብዙ ዜጎችንም ወደ እስር ቤት ወርውሯል። በርካቶች በደረሰባቸው ዘግናኝ ደበደባ አካለ ስንኩላን ሆነዋል። የብዙ አባወራዎች ቤት ተዘግቷል። ሌሎች በርካታ ወገኖቻችን ደግሞ ለስደት ተዳርገዋል።

ሰሞኑንም የአዲስ አባባ ከተማን ለማስፋፋት የወጣውን ማስተር ፕላን በመቃወም በሕገ-መንግሥቱ የተረጋገጠላቸውን መብታቸውን ተጠቅመው ሰላማዊ ሰልፍ በወጡ የከፍተኛ ተቋማትና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ላይ የተደረገው ግድያ የህወሓት/ኢህአዴግን አምባገነን ባህሪ በግልጽ አሳይቷል። በአሁኑ ጊዜ ተቃውሞው ከተማሪዎች አልፎ ሰፊውን ሕዝብ ያሳተፈ በመሆኑ፣ የግድያውም መጠንም ጨምሯል። የሕዝብን መብት በማፈንና በመግደል የተከፋንና የተገፋን የሕዝብ ዓመጽ የሚያቆሙት ይመስላቸዋል። ነገር ግን አፈናና ግድያ በጨመረ ቁጥር የሕዝብ አመጽም ከተዳፈነበት ገንፍሎ እንደ እሳተ-ገሞራ እምቁን ሰብሮ በመውጣት አምባገነኑን የእሳት ማዕበል ያላብሰዋል፤ ያቃጥለዋል፤ ብሎም ያወድመዋል። ይህ የታሪክ ሃቅ መሆኑን የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ከሌሎች አምባገነን አቻዎቹ ሊማር አልተቻለውም። ባህሪው ነውና ሊማር ከቶውንም አይቻለውም።

የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ በሄደ ቁጥር የመኖሪያ ቤት ፍላጎትን ለማሟላትና የከተማ ዕድገትን ተግባራዊ ለማድረግ፣ የየብስና ሌሎች የመገናኛ አውታሮችን ማስፋፋት የግድ ይላል። ለዚህ ሂደት ከተሞችን ማስፋፋት አስፈላጊ ስለሚሆን፣ በከተሞቹ ዙሪያ የሚገኙ ቦታዎችን ሊያካትት ይችላል። ይህ ሊሆን የሚገባው ግን ባለሥልጣናትን ወይም ሙሰኞችን ሆን ብሎ ለመጥቀም ሳይሆን፣ መስፋፋት ያለባቸው ከተሞችና የአካባቢውን ነዋሪዎች ጥቅምና ፍላጎት ከግምት

**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **Email Address: eprp-united@eprp-ihapa.com**

ውስጥ በማስገባት፣ የአካባቢውን ሕዝብ ያሳተፈና ሕዝቡ ያመነበት ምክክር ተካሂዶ፣ ስምምነት ላይ ሲደረስ ብቻ ሊሆን ይገባል። ሂደቱ ዋስትና ሊኖረው የሚችለውም፣ ሰላም፣ ዕድገትና ብልጽግና ሲረጋገጥ ብቻ ነውና ይህ ሳይሆን ቀርቶ ለሕዝብ መብት ደንታ የሌለው ሙሰኛና አምባገነን አገዛዝ የነዋሪዎችን መብት ረግጦ ከመኖሪያቸው የማፈናቀልና ንብረት የማውደም ተግባር ካካሄደ፣ ሂደቱ በፍፁም ሊወግዝ ይገባዋል።

በአሁኑ ወቅት፣ የተነሳሳውን ሕዝባዊ አመፅ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የህወሓት ከፋፋይ ፓሊሲ ሳይበግረው፣ በጎሣ፣ በሃይማኖትና በክልል ሳይከፋፈል በአንድነት ቆሞ አገዛዙን አስወግዶ የሁሉም ብሔረሰቦች እኩልነትና መብት የሚከበርባትን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እንዲገነባ ኢ.ሕ.አ.ፓ (አንድነት) ጥሪውን ያቀርባል።

በአለፉት ሃያ አራት ዓመታት በሕዝባችን ላይ ያለሕዝብ ፍላጎት ተግባራዊ እንዲሆን የተደረገው ዘውግን መሠረት ያደረገው አስተዳደራዊ መዋቅር ያደረሰውን ጉዳት ልብ ብለን ልናጤነው ይገባል። በጎሣ ምክንያት የሚነሳ እሳት ማንንም ሳይመርጥ ሁሉንም የሚለበልብ በመሆኑ ዋና ተዋናዩን ህወሓትን ጭምር እያቃጠለው ያለ መሆኑን ልብ ልንለው ይገባል። አያቶቻችንና ቅድመ-አያቶቻችን ጎሣና ሃይማኖት ሳይለያያቸው ከውጭ ወራሪ ጠላት ተከላክለው ያቆዩን አገራችን ኢትዮጵያ በህወሓት/ኢህአዴግ ፖሊሲ ምክንያት አደጋ ላይ ትገኛለች። <u>ከዚህ በፊት በነበሩ ሥርዓቶች ጭቆናና ብዝበዛ አልነበረም፤ አልተበዳደልንም ለማለት ከቶውንም አይቃጣንም። ነገር ግን ያለፈ በደል እንዳይደገም ሁሉንም አሳታፊና ሁሉንም በእኩልነት ሚዛን የሚያይ ሥርዓት በጋራ ገንብተን የጋራ የአገራችንን ህልውና እንጠብቅ ለማለት ነው።</u>

በአዲስ አበባና አካባቢዋ እስከ ወለጋና ሐረር ድረስ እንዲሁም በስሜን ምዕራብ በጎንደር በግፍ እየፈሰሰ ያለው የንፁኃን ደም አይቀሬውን ለውጥ ያፋጥነዋል እንጂ የህወሓትን ዕድሜ ከቶውንም አያራዝመውም። በዚህ ጭፍጨፋ ሕይወታቸውን ላጡ ወገኖቻችን ቤተሰቦች ሁሉ የተሰማንን ጥልቅ ኃዘን እየገለጽን፣ በዚህ አጋጣሚ አገዛዙን ከሥልጣን ለማስወገድ ለሚደረገው የዴሞክራሲያዊ ትግል ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን የቆምን መሆናችንን ልናረጋግጥ እንወዳለን።

ኢትዮጵያ አገራችን ለዘላላም ትኑር!

**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **Email Address: eprp-united@eprp-ihapa.com**